# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 112 ሐምሌ 1 ቀን 2002 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አገራዊና ሕዝባዊ የሆነን ትብብር በማስመልከት ጽሁፍ አወጣ

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ *እየደመቀ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና ሊሰጠው የሚገባ ምላሽ* በሚል ርእስ ባወጣው 22 ገጽ ጽሁፉ ችግሮቻችንን ለመቋቋም ተባብረን መቆም ባለመቻላችንና እነዚህንም ችግሮች ተባብረን ለማስወገድ የወሰድናቸው ተግባራዊ እርምጃዎች ባለመኖራቸው ከዓመት ዓመት እየገዘፉ መጥተው ዛሬ ሊውጡን ደርሰዋል ካለ በኋላ ጥምረቶቻችንን ዘላቂና ውጤታማ ማድረግ ባለመቻላችንም “ምንድነው የጎደለን?” ብለን ራሳችንን በጥብቅ መፈተሽ ይኖርብናል ብሏል።

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ያወጣው ጽሁፍ ዓላማ እነዚህን ጥያቄዎችና ጭንቀቶች ግምት ውስጥ ያስገባና በተወሰነ ደረጃ ለውይይት መነሻ የሚሆን መንደርደሪያ ሃሳብ ለማቅረብ መሆኑን ገልጾ እንደ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ እምነት፣ በደንብ ካሰብንበት፣ ከተዘጋጀንበትና ከደከምንበት የታለመለትን ግብ ሳይመታ የማይቆም በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚገኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ ድርጅቶችና በአስር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በአንድ ዓላማ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ አንዳንድ ከተሞች የሚገኙ የወያኔ ካድሬዎች፣ በአካባቢው እንደልብ መንቀሳቀስ እንደተሳናቸው ታወቀ

በተለይ በላይ አርማጭሆ፣ በጠገዴና በምእራብ አርማጭሆ ወረዳዎች ያሉ የወያኔ ካድሬዎችና ደጋፊዎች እንደቀድሞው በቀንም ሆነ በማታ ከከተማ ውጭ በመሄድ የበረሃ ስራ ለመስራት ከፍተኛ ስጋት ስላለባቸው እንቅስቃሴያቸው መገታቱን የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር በላከው ዘገባ አስታውቋል።

በምእራባዊ ወረዳዎች በላይ አርማጭሆ፣ በጠገዴ እና በምእራብ አርማጭሆ፤ እንዲሁም በዳንሻ፣ በባከር፣ በሁመራ ከተሞች እና በአካባቢው ከ12 ሰዓት በኋላ ከከተማ ውጭ መኪናም ሆነ ሰው መንቀሳቀስ የማይችል መሆኑ ታውቋል። ከጎንደር እስከ ሁመራና አብራጂራ ከተሞች የሚወስደው ዋና መንገድም ከ12 ሰዓት በኋላ ዝግ ሲሆን፤ በዚህ መስመር ያሉት ከተሞችም መሃል ለመሃል በኬላ ተዘግተዋል።

ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓም፣ በጠገዴ ወረዳ የሶሮቃ ከተማ ነዋሪ የሆኑ የወያኔ ካድሬዎች “በአሁኑ ጊዜ እንኳን በበረሃው በከተማውም የመኖራችን ተስፋ መንምኗል” እያሉ ሲነጋገሩ መደመጣቸውን ሪፖርተራችን ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ አዳዲስ አፋኝ እርምጃዎችን በስራ ላይ እያዋለ መሆኑ ተዘገበ

የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ የቀኝ እጅ የሆነው በረከት ስምኦን ቢሮ አዳዲስ አፋኝ እርምጃዎችን በስራ ላይ እያዋለ መሆኑ ተዘግቧል።

አዲስ ነገር ኦንላይን የተባለው የዜና ድረ-ገጽ በዚህ ሳምንት እንደዘገበው የበረከት ስምኦን ቢሮ በኢትዮጵያ ላይ በሚመራመሩ የውጭ አገራት ምሁራን ላይ በተለያዩ መንገዶች ጫና ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነው። አላማውም እነዚህ ተመራማሪዎች ወያኔ በኢትዮጵያ አለ ስለሚለው የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ፖሊሲ አዎንታዊ ነገሮች እንዲጽፉ ማድረግ ነው። አገዛዙ ከምርጫ 97 በኋላ የፈጸማቸውን የሰብአዊ መብት ረገጣዎች ለአለም ህዝብ ከማጋለጥ አኳያ የውጭ ተመራማሪዎች ከፍተኛ ሚና አላቸው ብሎ እንደሚያምን አዲስ ነገር ኦንላይን ዘግቧል።

ይኸው የዜና ድረ-ገጽ ባወጣው ዘገባ በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ስር በሚገኘው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት ቢሮዎች ውስጥ ካሜራዎች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ከኢትዮጵያውያን 44 ሚሊዮን ብር ዘርፎ የተሰወረው ግለሰብ ከወያኔ ጋር ትስስር አለው ተባለ

በደቡብ አፍሪካ ተገኝተው የአለም ዋንጫን ለመከታተል ለሚሹ ጉዞ አመቻቻለሁ በሚል ከበርካታ ኢትዮጵያውያን ገንዘብ ዘርፎ የጠፋው ግለሰብ ከወያኔ ጋር ትስስር እንዳለው ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ ገልጿል።

አስካሉካን የተባለው የንግድ ድርጅት ስራ አስኪያጅ የሆነው አቶ ግርማይ ገብረሚካኤል፤ ከ1200 ኢትዮጵያውያን ወደ 44 ሚሊዮን የሚጠጋ ብር ሰብስቦ አገልግሎቱን ሳይሰጥ መሰወሩ ተዘግቧል። ድርጅቱ አገልግሎቱን በሚያስተዋውቅበት ጊዜ ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት ድጋፍ እንዳለው የሚገልጹ ሰነዶችንም ለተጠቃሚዎቹ ማሳየቱን አዲስ ፎርቹን የተባለው ጋዜጣ ዘግቧል።

ምንም እንኳ ድርጅቱ ለተጓዦቹ በሙሉ ቪዛ እንደሚሰጥ ቃል ቢገባም፤ የደቡብ አፍሪካ ኤምባሲ አብዛኞቹ ተጓዦች ወደ ኢትዮጵያ አይመለሱም ብሎ በመጠራጠር መከልከሉ ታውቋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሂላሪ ክሊንተን የወያኔ አገዛዝ በአለም ላይ የሲቪሉን ማህብረሰብ እየረገጡ ካሉ አገዛዞች አንዱ ነው ሲሉ መሰከሩ

የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ ቢሮ ሃላፊ ሂላሪ ክሊንተን ሰሞኑን በፖላንድ ባደረጉት ንግግር፤ በወያኔ ቁጥጥር ስር ያለው የኢትዮጵያ መንግስት የሲቪል ማህበረሰቡን እየረገጡ ካሉ የአለም መንግስታት አንዱ ነው ብለዋል።

ወይዘሮ ክሊንተን፥ ማህበረሰባዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚገፉ እና የመንግስታትን ድክመት የሚያጋልጡ የዜጎች ማህበራት፤ የሃይማኖት ተቋማት፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት አፈና እየተደረገባቸው እንዳሉ መስክረዋል። “አፈናዎቹን ከሚያካሄዱት አገራት ውስጥ አንዳንዶቹ ዴሞክራሲያዊ ነን ይላሉ።” ያሉት ክሊንተን፤ “ዴሞክራሲያዊ መንግስታት ግን ህዝቦቻቸውን አይፈሩም። ይልቁንስ ዜጎቻቸው ለመሰባሰብ፤ ላመኑበት ለመሟገት እና ለመቀስቀስ ነፃነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ይረዳሉ” ብለዋል።

ፕሬዘደንት ኦባማ በበኩላቸው በዚሁ እለት በለቀቁት መግለጫ፥ በሲቪል ማህበረሰቡ ላይ እየተስፋፋ የሄደው ጥብቅ ቁጥጥር፤ ነፃነትን የሚሰጡ ሳይሆኑ የሚገድቡ ህጎች፤ እንዲሁም ዜጎች በመንግስታቶቻቸው ላይ እምነት እንዲያጡ እያደረገ ያለ ሙስና መስፋፋት የዩናይትድ ስቴትስን መንግስት እያሰጋው መሆኑን ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን በማስፋፋት ስም ከአለም ባንክ ብድር መቀበሉ ተዘገበ

የወያኔ አገዛዝ በጉልበት በተቆጣጠረው የኢትዮጵያ መንግስት ስም የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ወደ ገጠር መንደሮች በማስፋፋት ስም ከአለም ባንክ 180 ዶላር መበደሩ ተዘግቧል።

ባንኩ በበኩሉ ከሰማንያ ፐርሰንት በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የኤሌክትሪክ ሃይል እንደማያገኝ እና ይህ እጥረትም በአገሪቱ የኢኮኖሚን እድገት ወደ ኋላ እየጎተተ እንደሆነ በመግለጽ ይህ ገንዘብ ያንን ለማሻሻል እንደተሰጠ ተናግሯል።

ወያኔ በመሰረተ ልማት ግንባታ ስም ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ እርዳታና ብድር በየአመቱ እንደሚቀበል የሚታወቅ ሲሆን፤ ገንዘቡ ለተገቢው ስራ በአግባቡ መዋሉን ግን የሚቆጣጠር መንግስታዊም ሆነ ገለልተኛ ተቋም በአገሪቱ ውስጥ የለም። ከ4.7 ቢሊዮን ብር በላይ የወጣበት የግልገል ጊቤ ቁጥር ሁለት ግድብ አስፈላጊው ቅድመ ጥናት ሳይደረግበት ተገንብቶ ከተከፈተ በሳምንታት ውስጥ ግንቡ በመደርመሱ መዘጋቱ ይታወቃል።

ከዚህም በተጨማሪ፥ ዘረኛውና አምባገነናዊው አገዛዝ በቅርቡ የተከፈተውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን፣ የአሜሪካ ድምጽ ራድዮ እና የግንቦት 7 ድምጽ ራድዮን ጨምሮ ከውጭ የሚተላለፉ ገለልተኛ የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙሃን በአገር ውስጥ እንዳይሰሙ ለማፈን መጠኑ በውል (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## “ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ!”

ለመሆኑ ወያኔ አስመዘገብኩ ስለሚላቸው ስኬቶች ዓለም ዓቀፍ ገምጋሚዎች ምን ይላሉ? ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነትያላቸው ሶስት ዋና ዋና የስኬት ወይም የውድቀት መለኪያች ላይ እናተኩራለን።

**1. የጨነገፉ መንግሥታት መለኪያ**

ይህ መለኪያ በዓለም ያሉ የ177 አገሮች መንግሥታት ሕዝባቸውን በመምራት ረገድ ያሉባቸውን ድክመቶች በአስር ዋና ዋና መመዘኛዎች ይለካል። እነዚህም ሀ) ፈጣን የሕዝብ ብዛት የሚፈጥረው ውጥረት፣ ለ) የሕዝብ ከመኖሪያ ቦታው መፈናቀል፣ ሐ) የቡድኖች (የማኅበረሰብ) በሥርዓቱ መማረር፣ መ) ስደት፣ ሠ) አድልዖዓዊ የሆነ ልማት፣ ረ) የኢኮኖሚ ድቀት፣ ሰ) የመንግሥት በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማጣት፣ ሸ) የመንግሥት አገልግሎት አናሳነት፣ ቀ) የፀጥታ ኃይሎች ብቃት ማነስ፣ በ) የፓለቲካ ልሂቃን የእርስ በርስ መቆራቆስ፣ እና ተ) የውጭ ጣልቃ ገብነት ናቸው። ይህን ጥናት የሚያካሄደው የውጭ ፓሊሲና የሰላም ፈንድ የተባለ የምርምር ተቋም ሲሆን የምርምር ውጤቶቹ ከፍተኛ ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው።

በጨነገፉ መንግሥታት መለኪያ ዓለምን የምትመራው ጎረቤታችን ሶማሊያ ያገኘችው አጠቃላይ ነጥብ 114.3 ሲሆን ኢትዮጵያ በ98.8 አጠቃላይ ነጥብ 17ኛ ደረጃ ይዛ በቅርብ እርቀት ትከተላታለች። ለማነፃፀር ያህል ዩጋንዳ፣ ስሪላንካ፣ ብሩንዲ፣ ካሜሮን፣ ማላዊ፣ ቡርኪና ፋሶ እና ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተሻለ አስተማማኝ መንግሥታት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። ኢትዮጵያ ከዓመት ዓመት ያመጣችው መሻሻል ይኖር እንደሆን ለማጣራትያለፉትን ተከታታይ ዓመታት ውጤት ብናስተያይ በወያኔ መዳፍ ውስጥ ያለችው አገራችን በመሻሻል ፋንታ እየባሰባት እንደሆነ እናያለን። ሶማሊያን ጨምሮ እስከ ሃያኛ ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት መንግሥታት “የወደቁ መንግሥታት” የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል። ይህ ስያሜ በእነዚህ አገራት ውስጥ መንግሥት አለ ለማለት አያስችልም የሚል መልዕክት አለው። ወያኔ ሰላምና መረጋጋት ፈጠርኩ ብሎ የሚመፃደቅባት ኢትዮጵያ ከወደቁ መንግሥታት አንዷ ነች። ትርጉሙም ኢትዮጵያ ውስጥ “መንግሥት” ለመባል የሚበቃ ተቋም የለም ማለት ነው።

**2. በአፍሪቃ የመልካም አስተዳደር መለኪያ**

መለስ ዜናዊና አፍሪቃዊያን መሰሎቹ “የአቻ-ለአቻ ግምገማ” እያሉ እርስ በርስ እንደሚሞካሹ የታወቀ ነው። ይህ ሽፍጥ የአፍሪቃ አንድነትንም ሽባ ያደረገ ነው። በአሁኑ ሰዓት በገለልተኛነቱና በጥራቱ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘው የሞይ ኢብራሂም የአፍሪቃ የመልካም አስተዳደር መለኪያ ነው። ይህ ጥናት አገራቸውን በመልካም ሁኔታ አስተዳድረው ሥልጣናቸውን ለለቀቁ የአፍሪቃ መሪዎች 5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለመሸለም በተቋቋመ ተቋም የሚደረግ ምርምር ሲሆን አምስት ዋና ዋና መመዘኛዎች አሉት። እነዚህም ሀ) ደህንነት እና የህግ የበላይነት፣ ለ) የሕዝብ ተሳትፎ እና የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ሐ) ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ እና መ) ሰብዓዊ እድገት ናቸው። በየአመቱ 53 የአፍሪካ አገሮች በእነዚህ መመዘኛዎች ይለካሉ። ዘንድሮም ሽልማቱን ለመውሰድ የበቃ አፍሪቃዊ መሪ ባይገኝም ሞሪሰሽ፣ ኬፐቨርዲ፣ ሲሲሊ፣ ቦትስዋና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ናሚቢያ፣ ጋና፣ ቱኒዚያ፣ ሊሶቶ እና ሳኦ ቶሜና ፕሪንስ ከአንድ እስከ አስረኛ ደረጃ በመውጣት ተመስግነዋል። በወያኔ አገዛዝ ሥር ያለችው ኢትዮጵያ ግን 37ኛ በመሆን የመጨረሻው ረድፍ ላይ ትገኛለች። ለማነፃፀር ያህል ኬንያ፣ ዩጋንዳ፣ ሴራሊዮን፣ ሩዋንዳ፣ እና ጅቡቲ በመልካም አስተዳደር ረገድ ከኢትዮጵያ በተሻለ ሁኔታ ይገኛሉ። ሃቁ ይህ ሆኖ እያለ ነጋ ጠባ ስለ ስለአብዮታዊ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሚደሰኮርባት አገር ኢትዮጵያ መሆኗ መራር ምፀት ነው።

**3. የኢኮኖሚ ነፃነት መለኪያ**

ሄሪተጅ ፋውንዴሽን በዓለም ላይ ያሉ የ183 አገሮችን ኢኮኖሚዎችን በጥልቀት በመመርመር የቱን ያህል ነፃ መሆናቸውን ይለካል። ይህ ጥናት በሥራ ላይ ከዋለ ከአስራ አምስት ዓመታት በላይ የሆነው ሲሆን ኢኮኖሚዎች ምን ያህል ወደ ገበያ ኢኮኖሚነት እየቀረቡ አለያም ከዚያ እየራቁ እንደሆነ በመለካት ረገድ አቻ ያልተገኘት እና ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ መመዘኛ ነው። ይህ መለኪያ የኢኮኖሚ ነፃነትን በአስር የነፃነት አይነቶች ከፋፍሎ ይገመግማል። እነዚህም ሀ) የቢዝነስ ነፃነት፣ ለ) የኢንቬስትመንት ነፃነት፣ ሐ) የንግድ ነፃነት፣ መ) የበጀት ነፃነት፣ ሠ) የፋይናንስ ነፃነት፣ ረ) የንብረት ነፃነት፣ ሰ) የመንግሥት ወጪ፣ ሸ) ከሙስና ነፃ መሆን፣ ቀ) የገንዘብ ነፃነት፣ እና በ) የሥራ ነፃነት ናቸው።

በያዝነው የአውሮፓውያን 2010 ከዓለም ከሁሉም የተሻለ ነፃ ኢኮኖሚ ያላት አገር ሆንግ ኮንክ ስትሆን ያገኘችው አጠቃላይ ነጥብ 89.3 ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ 51. 2 አጠቃላይ ነጥብ በማምጣት 136ኛ ደረጃ ይዛለች። ይህ አጠቃላይ ውጤት ኢትዮጵያን “ኢኮኖሚያቸው ባብዛኛው ነፃ ያልሆነ” ከሚባሉ አገሮች ጋር መድቧታል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ነፃነት የጎደለው ብቻ ሳይሆን በመሻሻል ፋንታ እየባሰበት የመጣ ነው። ለምሳሌ 2009 ከነበረው ዘንድሮ በ1.8 ቀንሷል። ይህ የሚያመለክተው ወያኔ በኢትዮጵያ የገነባው የኢኮኖሚ ሥርዓትን የገበያ ኢኮኖሚ ነው ብሎ መጥራት የማይቻል መሆኑ ነው። አሁንም ለንጽጽር እንዲረዳን ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዛምቢያ፣ ኬኒያ፣ ማሊ፣ ሴሌጋል፣ ማላዊ እና ኮትዲቯር በኢኮኖሚ ነፃነት ከኢትዮጵያ በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ በርካታ የአፍሪካ አገሮች ጥቂቶቹ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩት ሶስት መመዘኛዎች ማጠቃለያ ግልጽ ነው። ወያኔ ጠንካራ መንግሥት አቋቁሜዓለሁ ብሎ ይኩራራል። ነገር ግን አገራችንን ከወደቁ መንግሥታት ተራ አሰልፏታል። የወያኔን መንግሥት በተነፋ ፊኛ የመሰሉ ሰዎች ምንኛ ትክክል ናቸው!!! ወያኔ ስለ መልካም አስተዳደር ነጋ ጠባ ይደሰኩራል፤ በተግባር ያሰፈነው ግን እጅግ መጥፎ የሆነ አስተዳደርን ነው። በመጨረሻም ወያኔ የገበያ ኢኮኖሚ ገንብቻለሁ እያለ የሚያደነቁረን ቢሆንም በተግባር የገነባው ግን ከገበያ ኢኮኖሚ ጋር ዝምድና የሌለው የሽፍቶች የዘረፋ ኢኮኖሚ ነው።

ይህን ያልነው እኛ ሳንሆን ከፍተኛ ሙያ፣ ዓለም ዓቀፍ ስምና ዝና ያላቸው፤ የራሳቸው መረጃዎችን አሰብሳብሰው በመሥራት የታወቁ ገለልተኛ አጥኚዎች ናቸው። ወያኔ የሰጣቸው ቁጥሮችን አማስለው የሚመጡ እና ባበደሩት ገንዘብ ስለተሠራ ስኬት የመስማት ረሃብ ያጠቃቸውን የዓለም ባንክና የአፍሪካ ልማት ባንክን ብቻ ከመስማት እውነትን ለማወቅ የሚጥሩ ገለልተኛ ተመራማርዎችን ማድመጥ ተገቢ ነው። ወያኔን “ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ” የተባለውን የአገራችንን ምሳሌ እናስታውሰዋለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## አንዳንድ የሰሜን ኢትዮጵያ ነዋሪዎች ከወያኔ ካድሬዎች መሳሪያ እየነጠቁ በረሃ መግባት መጀመራቸው ታወቀ

የወያኔን ግፈኛ አገዛዝ በትጥቅ ትግል ለመታገል የቆረጡ የሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ ነዋሪዎች ከአገዛዙ ሚሊሻዎች ትጥቅ እየቀሙ ጫካ እስከመግባት መድረሳቸውን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ዘገባ አመልክቷል።

በሰሜን ኢትዮጵያ ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በኋላ በርካታ ወጣቶች እና ጎልማሶች ቀያቸውን ጥለው በትጥቅ ትግል ወደሚፋለሙት ተቃዋሚዎች ጎራ እየሄዱ መሆናቸው ታውቋል። በአብዛኛው ከጠገዴ፣ ከምእራብ አርማጭሆ፤ ከቋራ፤ ከመተማ፤ ከዳባትና ደባርቅ ወረዳዎች፤ እንዲሁም ከባህርዳርና አካባቢው የአገር አንድነትና ነፃነት የጠማቸው በርካታ ዜጎች ወደ በረሃ በመግባት ለቁርጠኛው ትግል መሰለፋቸውን የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአካባቢው ባስተላለፈው ዘገባ ገልጿል።

አንዳንድ ዜጎችም ከወያኔ ታጣቂዎች፣ በተለይም ከአካባቢው ሚሊሻዎች፣ ካድሬዎችና ደጋፊዎች የታጠቁትን መሳሪያ እየነጠቁ በአካባቢው ወደሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ሃይሎች እየተቀላቀሉ መሆናቸው ታውቋል። ሰኔ 15 ቀን 2002 ዓም በጠገዴ ወረዳ ማርዘነብ በሚባል የገጠር ቀበሌ በቡድን የተደራጁ ዜጎች ከወያኔ ሚሊሻዎች AK 47 ወይም ክላሽ የተባለውን መሳሪያ ነጥቀው ወደ በረሃ መግባታቸውን ሪፖርተራችን ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል። ይህም ድርጊት በአካባቢው የወያኔ አስተዳደር ላይ ከፍተኛ መሸበርን እንደፈጠረ ለማወቅ ተችሏል።

## የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ስር የሚተባበሩበት የፀረ-ወያኔ የተባበረ እንቅስቃሴ መፍጠር ይቻላል። በአገራችን ድርጅቶች መካከል የሚደረግ የስምምነት ውል የሚያፀናው 1) የድርጅቶችና መሪዎቻቸው ቀና ፍላጎትና አርቆ አሳቢነት፤ 2) በተወሰን ደረጃም ቢሆን በሕዝብ ፊት የተገባ ቃል ኪዳንና ፤ 3) ውሉን በሂደት ለማፍረስ ሰበብ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ማናቸውም ችግሮች አስቀድሞ የታሰበባቸውና መፍትሄ የተሰጣቸው ከሆኑ ብቻ ነው ብሏል።

በመጨረሻም ይህንን ሃቅ ከምር በመረዳት የግንቦት7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አገራዊና ሕዝባዊ ለሆነው የመተባበር ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑን በጽሁፉ ውስጥ የተቀመጡትን እና ከሌሎች ወገኖች ጋር በሚደረጉ ምክክሮች የሚታከሉ ቁምነገሮችን የመተባበሪያዎችን መሠረት አድርገን ከተነሳን የተዋጣለት ትብብር በማድርግ የወያኔን ዘረኛና አምባገነናዊ ሥርዓት እድሜ እናሳጥራለን በማለት አጠቃልሏል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የማይታወቅ ነግር ግን ከፍተኛ እንደሆነ የሚገመት የኤሌክትሪክ ሃይል ያባክናል።

የወያኔ አገዛዝ እስከዚህ አመት አጋማሽ ድረስ ወደ 66 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ በኢትዮጵያ ስም መበደሩን ያስታወቀ ሲሆን፤ በሚቀጥለው አመት በከፍተኛ መጠን እንደሚጨምር ሐሙስ እለት ለመጪው አመት የጸደቀው በጀት ጠቁሟል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# እየደመቀ የመጣው የሕዝብ የተባበሩ እሪታና ሊሰጠው የሚገባ ምላሽ

**በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ የተዘጋጀ: ሐምሌ 2002 (ክፍል 1)**

## 1. *መግቢያ*

ስለ መተባበር ጠቀሜታ በመዘርዘር ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም። በአገራችን ለዘመናት የተንሰራፋው የግፍ አገዛዝ ያፋፋቸው እና እኛንም በዓለም ፊት እያዋረዱን ያሉት ድህነት፣ ችጋር፣ በሽታና ማይምነት ከመቸውም በላይ ህልውናችንን እመፈታተን ደረጃ ላይ የደረሱት ችግሮቻችንን ለመቋቋም ተባብረን መቆም ባለመቻላችን እንደሆነ አከራካሪ ጉዳይ አይመስለንም። እነዚህን ችግሮች ተባብረን ለማስወገድ የወሰድናቸው ተግባራዊ እርምጃዎች ባለመኖራቸው ከዓመት ዓመት እየገዘፉ መጥተው ዛሬ ሊውጡን ደርሰዋል። ከዚህ በፊት በርካታ የመተባበሪያ መልካም አጋጣሚዎችን አባክነናል። ሌላው ሁሉ ቀርቶ ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ውስጥ ከመተባባበር ውጭ ዘረኛውና አምባገነኑን ወያኔን በተበታተነ ኃይል ማስቆም እንደማይቻል ሁላችንም አውቀናል። የአብሪተኛው የጥቂቶች አገዛዝ ህልውና የቆመው "በከፋፍለህ ግዛ" መርህ መሰረት መሆኑን በተግባር አይተነዋል:: ለዚህም ነው ባለፉት አስር ዓመታት ኢትዮጵያዊያን በተሰበቡበት መድረክ ሁሉ "እባካችሁ ተባብረን እንቁም" የሚሉ የተማፅኖ ንግግሮች መስማት የተለመደ የሆነው። ነገር ግን የመተባበርን ጥቅም መረዳት ብቻውን መተባበርን አይፈጥርም። ሆድን የሚያባቡ "የእንተባበር" ተማፅኖዎች በተግባር እስካልተደገፉ ድረስ ውጤታማ አይሆኑም።

እርግጥ ነው በእነዚህ ዓመታት ከቃላት የዘለሉ የትብብር ሙከራዎች ተደርገዋል። የድርጅቶች ጥምረት ለመፍጠር ተሞክሮ ጥቂት እርምጃዎችን ተጋግዘን የተጓዝንባቸው ጊዜዓት ነበሩ። ሆኖም ግን የፈጠርናቸውን ጥምረቶች ዘላቂ እና ውጤታማ ማድረግ ባለመቻላችን እርቀው ሳይሄዱ ተደነቃቅፈው ወድቀዋል። ተጋግዘን ወደፊት ከተጓዝነው በላይ ተናቁረን ወደኋላ የምንመለስበት በመብዛቱ ሕዝባችን በብሩህ ተስፋ እና በተስፋ መቁረጥ መካከል እንዲንገዋለል ተፈርዶበታል። ጥምረቶቻችንን ዘላቂና ውጤታማ ማድረግ አልቻልንም። "ምንድነው የጎደልን?" ብለን ራሳችንን በጥብቅ መፈተሽ ይኖርብናል።

ሰሞኑን የመተባበር ጥሪ ከመቼውም በላይ ጎልቶ እየተስተጋባ ነው። ጥሪውን የጎላ ያደረገው ወያኔ ከዚህ ቀደም የማናውቀውን ባህርይ ስላሳየን ወይም የማንጠብቀውን ድርጊት ስለፈፀመ አይደለም። ወያኔ የፈፀመው ምን የማይታወቅና የማይገመት ነገር አለ? የሰሞኑን የመተባበር ጥሪ የቀሰቀሰው ወያኔ በቅርቡ ምርጫ ብሎ በከወነው ትዕይንት በፈጸመው ሸፍጥ የፓርላማውን ወንበር 99.6% በመውሰዱ ምክንያት ነው ብሎ መገመት የተሳሳተ ይመስለናል። ወያኔ ከዚህም የከፋ ነገር ከማድረግ የማይመለስ እኩይ መሆኑን ብዙዎች ኢትዮጵያዊያን እናውቃለን።

አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ያንገበገበው "በምርጫ 2002" አማካይነት ወያኔ ለሁላችንም በጉልህ ያስተላለፈው መልዕክት ነው። ንቀት!!! እጅግ አዋራጅ የሆነ ንቀት!!!! "የምርጫው" ሂደትና የተጠናቀቀበት መንገድ ወያኔ ለሁላችንም ያለውን ንቀት ያለምንም መሸፋፈን በአደባባይ የገለጸበት እብሪት ነው። ከወያኔ ጋር የገጠምነው ትንቅንቅ ከዴሞክራሲ፣ ከመልካም አስተዳደር፣ ከአገር ጥቅምና ደህንነት በላይ ተሻገሮ ሰው በመሆናችን በእያንዳንዳችን ሰብዓዊ ክብር ዙሪያ የሚያጠነጥን መሆኑን መረዳታችን ነው ሰሞኑ ብዙዎቻችንን በጋራ ቁጣ እንድንተሳሰር ያደረገን። ቻል ብለነውና ትተነው የነበረውን የጋራ ትግል ጥያቄ የቀሰቀሰው ይህ የያንዳንዳችንን አጥንት ዘለቆ የገባ እንደሰው በክብር ሳይሆን እንደሻገተ አተላ በወያኔ እየተደፋ ያለው ስብዕናችን ነው። "መረረኝ!!! አሁንስ በቃኝ!!! ከዚህ በኋላ ከወገኖቼ ጋር ተባብሬ ይህንን የግል ውርድት ማስቆም ይገባኛል!" የሚል እምነት ነው የዛሬውን የመተባበር ፍላጎት የሚገፋው። ዛሬ ሁላችንም ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከደሃ እስከ ሃብታም፣ በአገር ውስጥ ሆነ በስደት ኗሪ በሙሉ ወያኔ ባሰረልን የባርነት እግረ ሙቅ መታሰራችን ፍንትው ብሎ እንዲታየን የተደረገበት ወቅት ነው። ይህ ሃቅ ነው እንግዲህ የመተባበርን ጉዳይ እንደገና ወደ መድረክ ገፍተሮ ያወጣው።

"ምርጫ 2002" ከመተባበር አስፈላጊነት በተጨማሪ ለመተባበር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። የወያኔ እብሪተኛ ድርጊት ወያኔን እንቃወማለን በሚሉ ድርጅቶች መሃል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የነበሩ ልዩነቶችን ትርጉም አሳጥቷቸዋል። የ2002 ምርጫ "ወያኔ ሊሻሻል ይችላል ወይንስ አይችልም?" "ወያኔን መታገያው ስልት ሰላማዊ ነው ወይንስ የአመጽ?" በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የነበሩ መናቆሮችን አስቁሟል። ሁሉም በሚያምቸው የትግል ስልት እና እርስ በርስ በተደጋገፈ መንገድ ወያኔ ላይ በጋራ ከመነሳት የተሻለ አማራጭ እንደሌለ አሳይቶናል።

አሁን የቀረን "እንዴት አድርገን ነው ኃይላችንን፣ እውቀታችንን ገንዘባችንን አስተባብረን የወያኔን እድሜ የምናሳጠረው?" የሚለው አጀንዳ ብቻ ነው። በወያኔ መረገጥ የተማረረው ሕዝብም ሆነ የተቃዋሚ ድርጅቶች ካለፉ የመተባበር ተመክሮዎች በመነሳት "ጊዜው የሚጠይቀውን ጥብቅ ትብብር ለማሳካት እንዴት እንችላለን?" የሚል ጥያቄ ማንሳት ጀምሯል። የወደፊቱ ትብብር እንዳለፉት ትብብሮች የታለመለትን ግብ ሳይመታ እንዳይቀር ምን መደረግ ይኖርበታል በማለት መጨነቅ ጀምረዋል። የዚህ ጽሁፍ ዓላማ እነዚህን ጥያቄዎችና ጭንቀቶች ግምት ውስጥ ያስገባና በተወሰነ ደረጃ ለውይይት መነሻ የሚሆን መንደርደሪያ ሃሳብ ለማቅረብ ነው።

እንደ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ እምነት፣ በደንብ ካሰብንበት፣ ከተዘጋጀንበትና ከደከምንበት የታለመለትን ግብ ሳይመታ የማይቆም በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚገኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተለያዩ ድርጅቶችና በአስር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በአንድ ዓላማ ስር የሚተባበሩበት የፀረ-ወያኔ የተባበረ እንቅስቃሴ መፍጠር ይቻላል። ይህን የተቀደሰ ሃሳብ ለማሳካት ግን ብዙ ጥያቄዎችን አንስተን በአጥጋቢ ሁኔታ መመለስ ይጠበቅብናል። ይህ ጽሁፍ ስለመተባበርና ስለድርጅቶች ጥምረት ዋና ዋና ነጥቦችን ካነሳና የዓለም ዓቀፍ ልምድንም ከዳሰሰ በኋላ ወደአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመመለስ እስካሁን **ምን ተሰራ፣ ምን ጎደለ ? ወደፊትስ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል? በሚሉ ነጥቦች ላይ ያተኩራል።** የያዝነው ርዕስ ሰፊና ሞጋች ቢሆንም በጥቂት ገፆች ለመወሰን መጣራችንን ትገነዘቡልናላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

## 2. መተባበር መቻል ጥበብ ነው

ከላይ እንደተጠቀሰው ስለመተባበር ጥቅም ማውራት እምብዛም ፋይዳ የለውም፤ የታወቀ ነው። ይልቁንስ "ሰዎች የመተባበርን ጥቅም እያወቁ የማይተባበሩት ለምንድነው?" የሚለውን "እንቆቅልሽ" መፍታት እጅግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ሰዎች መተባበር የማይፈልጉባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። መተባበር ፈልገው እያለም ከመተባበር የሚያግዷቸው ሌሎች በርካታ ምክንያቶች አሉ። ሶስት ዋና ዋና ችግሮችን እናንሳ

### 2.1 የማስተባበር ችግር

ተባብሮ ለመሥራት ፍላጎትም ዝግጁነትም ኖሮ እያለ በአስተባባሪ እጦት ምክንያት ትብብር ተግባራዊ ላይሆን ይችላል። እዚህ ላይ "አስተባባሪ" ሲባል ሰውንም ተቋምንም ይመለከታል። **የኅብረት ሥራ ህግ፣ ሥርዓትና ድርጅት ይጠይቃል። በጋራ የሚሠራ ሥራ ማን ምን እንደሚሠራ እና ሥራው መሠራቱ የሚቆጣጠረው ማን እንደሆነ ግልጽ ተደርጎ ካልተጀመረ "እንተባበር" ስለተባለ ብቻ ኅብረት አይመጣም።** በስፖርት - ለምሳሌ - የቡድን አባላት በጨዋታው ዓይነትና ህግ መስማማት አለባቸው፤ ቀጥሎ ደግሞ ኃላፊነቶችን መከፋፈል ይኖርባቸዋል። ለእግር ኳስ የተገናባ ቡድን ለመረብ ኳስ አይሆንም። ግልጽ የሆነ ዓላማ፣ ደንብና መዋቅር የመኖሩ አስፈላጊነት በሁሉም የኅብረት ሥራዎች ውስጥ የማይቀር ነገር ነው። በዚህ ረገድ በስፓርትም፣ በእድርም፣ በፓለቲካ ፓርቲዎችም ዘንድ ያለው ችግር ተመሳሳይ ነው።

ይህ ችግር ለመፍታት የሚያስፈለጉ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አመራርና /leadership/ እና ማኔጅመንት ናቸው። በዚህ ረገድ ባህል እጅግ ከፍ ያለ ሚና ያለው፤ በአጭር ጊዜ ለመቀየር የሚያስቸግር ነገር ነው። በባህል ጉዳይ ወደ ኋላ እንመለስበታለን።

### 2.2 የመተማመን እጥረት

የኅብረት ሥራዎች ትልቁ ችግር አብረው ለመቆም በተስማሙ አባላትና አካላት መካከል ያለው የመተማመን ደረጃ ለኅብረቱ ፍሬያማ ውጤት ወሳኝ የመሆኑ ክፋት ነው። በተወሰነ መጠን ቢሆንም እንኳን በገበያ (በኢኮኖሚ) ሳይተማመኑ መተባበር ይቻላል። **በፓለቲካ ውስጥ ግን ሳይተማመኑ ለመተባበር ያለው እድል እጅግ የጠበበ ነው። "ያዛልቀኝ ይሆን?" ወይስ "ይከደኝ ይሆን?" የሚለው ጥርጣሬ በጋራ ሥራ ላይ ጊዜ፣ እውቀትና ሃብት ላለማፍሰስ ሰበብ ሊሆን ይችላል።** የመተማመንን እጥረት ለማስወገድ የሚረዳ አስተማማኝ መፍትሄ ባይኖርም የሚከተሉት ነጥቦች ጠቃሚ ናቸው ተብሎ ይገመታል።

2.2.1 በተቻለ መጠን ሁሉም ተሳታፊዎች የኅብረቱ ተጠቃሚዎች ማድረግ፤

2.2.2 ለአባል ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ስምና፣ ክብር ከፍ ያለ ዋጋ መስጠት (ግለሰቦችም ተቋማትም የገነቡትን መልካም ስምና ዝና /reputation/ እንዳያጡ ለውሎች ታማኝ ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል)፤

2.2.3 ስምምነቶች ሁሉ በተቻለ መጠን በጽሁፍ እንዲሆኑ ማድረግ፤

2.2.4 መሪዎችን ውል የማፍረስ አቅም ማሳጣት። ውል በቀላሉ እንዳይፈርስ በመተዳደሪያ ማጥበቅ፤ እና

2.2.5 ትብብርን በትናንንሽና ለማስፈጸም ቀላል በሆኑ ጉዳዮች ጀምሮ ደረጃ በደረጃ ማሳደግ።

### 2.3 በግል ኪሳራና እና በጋራ ጥቅም መካከል ያለው ተቃርኖ

ከኅብረት ሥራ የጋራ ጥቅም ቢገኝም በግል የሚያመጣው ጉዳትም አለ። እያንዳንዱ ተሳታፊ ከጋራ ጥቅም ለመጠቀም፤ ከግል ጉዳት ደግሞ ለመሸሽ ቢጥር የሚገርም ሊሆን አይገባም። ይህ የተለመደ የሰው ልጅ ባህርይ ነው። እያንዳንዱ ሰው ጥቅምና ጉዳቱም ማመዛዘኑ ተፈጥሯዊ ነው። ለኅብረት ሥራ ይኸ ተቃርኖ ችግር የሚሆነው የሥራው ውጤት በልፋት መጠን ማከፋፈል በማይቻልበት ወቅት ነው። ብዙዎቹ የኅብረት ሥራ ውጤቶች ጭራሹኑ የማይከፋፈሉ ናቸው። በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ጭምት ነኝ ባይ ራሱ እያሸሸ በድካም የተገኘውን ውጤት ለመካፈል ግን ቀድሞ ተሰላፊ ይሆናል።

(ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

## መለስ ዜናዊ ለመጪው አመት ያወጣው በጀት የአገሪቱ የእርዳታ ጥገኝነት እንደቀጠለ መሆኑን አሳየ

በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ማግስት የምእራባውያን አገራት እርዳታ አያስፈልገንም ብሎ ሲፎክር የነበረው መለስ ዜናዊ፤ በፓርላማው ያስጸደቀው የመጪው አመት በጀት አርባ በመቶ ያህሉ ከውጭ አገራት በሚገኝ እርዳታ እና ብድር እንደሚሟላ ታውቋል።

መለስ ዜናዊ በምርጫው ተውኔት ሰሞን ለጋዜጠኞች በሰጠው ቃል፤ በምርጫው ሂደት ደስተኞች ያልሆኑ ምእራባውያን አገራት ከፈለጉ የእርዳታ ገንዘባቸውን ይዘው መሄድ ይችላሉ ብሎ መፎከሩ ይታወሳል። ሰኔ 24 ቀን ሐሙስ እለት ለፓርላማ ቀርቦ የጸደቀው በጀት 77.2 ቢሊየን ብር ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 36 ቢሊዮን ብር የሚሆነው በእርዳታ እና በብድር ሊገኝ የታቀደ መሆኑ ተነግሯል። በፓርላማው ባሉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በተለይም ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ሂደት በኋላ ያንን ሁሉ ገንዘብ ከውጭ አገኛለው ብሎ እንዴት እንደተማመነ የተጠየቀው መለስ፤ "ይህ ገንዘብ እጃችን የማይደርስበት አንድም እድል የለም" ብሏል።

ለመጪው አመት የጸደቀው የበጀት መጠን ከምን ጊዜውም በላይ እንደሆነ ተደርጎ በአገዛዙ መነገሩን አስመልክቶ ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየት የሰጡ የኢኮኖሚክስ ምሁር፤ የተሰጠው ቁጥር የአመቱን የዋጋ ግሽበት ከግምት ያላስገባ እንደሆነ እና እውነተኛ ዋጋው ካለፈው አመት በጀት እኩል ወይም ያነሰ እንደሚሆን ገልጸዋል።

አንዳንድ የኢኮኖሚ ተንታኞች አገዛዙ እንዳቀደው እርዳታ እና ብድር አግኝቶ በጀቱን ማሟላት ካልቻለ እንደከዚህ ቀደሙ አገሪቱ የሌላትን ገንዘብ እያተመ በገበያው ላይ በመድፋት በህዝቡ ላይ የባሰ የዋጋ ንረት ይጭናል የሚል ስጋት እንዳላቸው ይናገራሉ።

### ከኢትዮጵያውያን 44 ሚሊዮን ብር ዘርፎ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አንዳንዶቹ ተጎጂዎች ክፍያውን ለመፈጸም ንብረታቸውን መሸጣቸውን አዲስ ፎርቹን ዘግቧል። ከ1200ዎቹ አንዱ የሆነው እና ይድነቃቸው አበበ የተባለ ከደቡብ ክልል የመጣ ገበሬ የእርሻ መሬት መብቱን ሸጦ 37 600 ብር ለግርማይ ገብረሚካኤል መክፈሉ ተጠቅሷል። ገበሬው በአሁኑ ጊዜ ወደ መንደሩ እንኳ መመለሻ አጥቶ ከሰው እየለመነ እንደሚበላ እና ውጪ እንደሚያድር ለዜና አውታሩ ገልጿል።

ይድነቃቸው እና ጋዜጣው ያነጋገራቸው አብዛኞቹ ተጎጂዎች እውነተኛው አላማቸው እግር ኳስ ማየት ሳይሆን በደቡብ አፍሪካ ቀርተው የተሻለ ኑሮ ማፈላለግ መሆኑን አምነዋል።

አስካሉካን የወያኔ ንብረት የሆነው ኤፈርት ኩባንያ የእጅ አዙር ንብረት መሆን አለመሆኑ ባይረጋገጥም፤ ባለቤቱ ግርማይ ገብረሚካኤል ግን ከገዢው ቡድን ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለው የደረሰን መረጃ ገልጿል።

### ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መተከላቸውን አስታውቋል። ይህም የተደረገው ሰራተኞቹ በነፃነት እርስበርስም ሆነ ከውጭ አካላት ጋር እንዳይነጋገሩ ለመገደብ ነው ሲሉ አንዳንዶች እንደሚያምኑ ዘገባው ገልጿል።

ከዚህ ቀደም ከገዢው ፓርቲ ጋር የቅርብ ትስስር የነበረውን ሃይለእየሱስ ወርቁን ጨምሮ ሁለት የኢትዮጵያ ራድዮ ጋዜጠኞች ለአንድ የውጭ አገር የዜና ድርጅት የወያኔ ጦር በሶማሊያ ሲቪል ዜጎችን ሲገድል የሚያሳይ ቪዲዮ ለመሸጥ ሲስማሙ ተያዙ በሚል መታሰራቸውን ድረ-ገጹ አስታውሷል።

አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በራስ መተማመኑ እየቀነሰ እና ስጋቱ እየጨመረ በሄደ ቁጥር እንደዚህ ያሉ አፈናዎችን እና ቁጥጥሮችን ማስፋፋቱን እንደሚቀጥል አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

### ሂላሪ ክሊንተን የወያኔ አገዛዝ በአለም ላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ወ/ሮ ክሊንተን በንግግራቸው፥ የእንግሊዙ መሪ ዊንስተን ቸርችል ከስልሳ አመታት በፊት በአውሮፓ ላይ የነሐስ መጋረጃ እየወረደ ነው ሲሉ የተናገሩትን አስታውሰው፤ ምንም እንኳ ያ የነሃስ መጋረጃ ከሶቪየት ህብረት መውደቅ በኋላ ቢወገድም፤ አሁን ደግሞ በአለም ዙሪያ ያሉ አንዳንድ መንግስታት የሲቪሉን ማህበረሰብ እና የሰው ልጆችን መንፈስ ለማድቀቅ እየተጠቀሙበት ስላለው የብረት ማነቆ ልንሰጋ ይገባናል ብለዋል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ በየአመቱ በሚያወጣው ሪፖርት ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚፈጽመውን የሰብአዊ መብት ረገጣ ቢዘረዝርም፤ ይህ ግን አስተዳደሩ በወያኔ ላይ የሚከተለውን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከመለወጥ አኳያ እስካሁን ያደረገው ተጽእኖ እንደሌለ ይታወቃል።

## የሰሜን ምእራብ ኢትዮጵያ ነዋሪዎች የአገሪቱን ድንበር ለመጠበቅ እየተዋጉ ነው፤ አንድ ኢትዮጵያዊ ሞቶ ሁለት መቁሰላቸው ታወቀ

ሰኔ 15፣ 2002 ዓም በአገራቸው ወታደሮች የተደገፉ ሱዳናውያን ዜጎች በሰሜን ጎንደር ዞን በምእራብ አርማጭሆ ወረዳ በኮርሁመር ቀበሌ በኩል ድንበር ጥሰው በመግባት የአንድ ባለሃብት የእርሻ ካምፕና አጠቃላይ ንብረቱን ሲያቃጥሉ፣ አንድ ኢትዮጵያዊ ገድለው ሁለት ማቁሰላቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አሳውቋል።

በዛው አካባቢ ከግንቦት 17 – 22 ቀን በተደረገ ተመሳሳይ ግጭት 2 ሱዳናውያን ሞተው ከሁለቱም ወገን 10 ሰዎች መቁሰላቸውም ታውቋል።

የወያኔ አገዛዝ ከሰሜን ምእራብ ጫፍ ከሉጉዲ እስከ ጋምቤላ ክልል ድረስ ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር እና ስፋቱ 30 ኪሎሜትር የሆነ መሬት ለሱዳን መስጠቱ ይታወሳል። ይህ መሬት በአየር ቢካለልም፣ በአካባቢው ህዝብ አይበገሬነት እና አገዛዙም የግንቦቱን የምርጫ ተውኔት በጸጥታ ለማከናወን ካለው ፍላጎት የተነሳ በመሬት ላይ የማካለል ስራ እስካሁን አልተሰራም።

በወታደሮች እየታገዙ ወዳካባቢው የሚዘልቁት ሱዳናውያን ከመተማ እስከ ወከዲ 300፣000 ሄክታር መሬት እንዳላቸው በማሳወቅ ኢትዮጵያውያኑ እንዲወጡላቸው መጠየቃቸው ታውቋል። ኢትዮጵያውያኑ የመሬታቸውን አልፎ መሰጠት በመቃወም ትግልን መምረጣቸው የታወቀ ሲሆን፤ የወያኔ አገዛዝም እንደተጠበቀው ከሱዳናውያኑ ጎን በመቆም አካባቢውን ጥለው እንዲወጡ እየገፋ ነው። ወያኔ ግንቦት 22 ቀን ሱዳናውያንን ገድላችኋል በሚል ያሰራቸውን ኢትዮጵያውያን በጠገዴ ወረዳ በምትገኘው ሶሮቃ በተባለች ከተማ እስር ቤት አጉሮ እያሰቃያቸው እንደሆነም ከስፍራው የደረሰን መረጃ ጠቁሟል።

የስፍራው የወያኔ ሹማምንት የመሬት ርክክቡ በቅርቡ እንደሚከናወን ሲናገሩ ቢደመጡም፤ አገዛዙ ግን ባጠቃላይ አካባቢውን መቆጣጠር ተስኖት እንደቆየ ለማወቅ ተችሏል። ግጭቱ ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ ሲሆን፤ በአካባቢው የበጎ አድራጎት ስራ የሚሰጠው ድንበር የለሽ ሃኪሞች ወይም ሜዲሲን ሳን ፍሮንቲየ የተባለው አለማቀፍ ድርጅት መንቀሳቀስ አለመቻሉን ምንጮች ለዘጋቢያችን ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜናም ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የጸጥታ ሃይል የሰሜናዊ ምእራብ በረሃን መቆጣጠር እንዳቃተው ታወቀ። ወያኔ በሰሜን ምእራብ አቅጣጫ በተለይ በሳንጃ፣ በዳንሻ፣ በባከርና በሁመራ ከተሞችና በአካባቢው ከፍተኛ ጦር ያከማቸ መሆኑ ቀደም ሲል መዘገቡ ይታወሳል።

ይህ ቀጠና በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ የታጠቁ ተቃዋሚዎች የሚንቀሳቀሱበት በመሆኑ፤ አገዛዙ ሰላይ ወይም ቃኚ ወታደሮችን አስርጎ ከማስገባት በስተቀር አብዛኛውን የሰሜን ምእራብ በረሃ መቆጣጠር እንደተሳነው ምንጮች ገልጸዋል።

ወያኔ ዋናው የበረሃ እምብርት የሚባለውን ይህንን ወታደራዊ ቀጠና መቆጣጠር ባለመቻሉ በአሁኑ ጊዜ ከአበራጂራ እስከ ሶሮቃ እና ከሁመራ እስከ ጎንደር ከተማ ድረስ ያለውን ዋና የመኪና መንገድ ብቻ በትናንሽ ቡድኖች ወይም ጋንታ በተከፋፈለው ሰራዊቱ በተበታተነ ሁኔታ በማስጠበቅ ላይ መሆኑን በአካባቢው የሚገኘው የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ለመረዳት ችሏል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org